# ኬንሲንግተን ክሊኒክ

## ቀጠሮ ስለመያዝና ቀጠሮዎን ስለማረጋገጥ

ቀጠሮዎች ሁሉ ማስወረድ እንዲደረግላቸው በሚጠይቁት ሴት የስልክ ጥሪ መመዝገብ አለባቸው፡፡ በሦስተኛ ወገን የሚደረጉ ቀጠሮዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው የቋንቋ ችግር ካለ ብቻ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ጥሪው በሚደረግበት ወቅት ማስወረዱን የሚፈልጉት ሴት እዚያ መኖር አለበቸው።

በሚደውሉበት ጊዜ እባክዎ የጤና መድን ቁጥርዎ እና ቀደም ሲል ለመጨረሻ ጊዜ ያዩት መደበኛ የወር አበባ የተከሰተበትን የመጀመሪያ ቀን ለመንገር ያዘጋጁ፡፡ ተገቢውን እንክብካቤ ልናደርግልዎ እንችል ዘንድ ስላሉብዎት የጤና ችግሮች፣ ተላላፊ በሽታዎችና ስለማይስማሙዎት መድኃኒቶች ለኛ መግለጽዎ ዋና ነገር ነው፡፡

ወደ ክሊኒኩ ከመምጣትዎ አስቀድመው የደም ምርመራ ማድረግ አለብዎ፡፡ ምርመራውን ክሊኒኩ ያዘጋጅልዎታል፡፡

ለመጨረሻ ጊዜ የወር አበባ ያዩበትን ጊዜ ካላስታወሱ ወይም ከ12 ሳምንታት በላይ በእርግዝና ከቆዩ ወይም ከካልጋሪ አካባቢ ውጭ የሚኖሩ ከሆነ፤ ከቀጠሮው በፊት የአልትራሳውንድ ምርመራ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡፡ ምርመራውን እዚህ ክሊኒክ ወይም በግል ዶክተርዎ አማካኝነት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡

**<u>ቀጠሮን ስለ ማረጋገጥ</u>**

ቀጠሮዎን ለማረጋገጥ ለእኛ ስልክ የሚደውሉበትን ቀን እንገልጽልዎታለን፡፡ በዚህ ቀን ከእኩለ ቀን በፊት መደወል አለብዎ፡ ይህ ካልሆነ ቀጠሮው ወዲያው ይሰረዛል፡፡ ማስወረዱን ከማድረግዎ በፊት ሊከተሏቸው የሚገቡ መረጃዎችና መመሪያዎች ከታች ተዘርዝረዋል፡፡

- ከቀጠሮው አስቅድሞ ባለው 5 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አንዳችም ምግብ ወይም መጠጥ ሊወስዱ አይችሉም። የመጡት ለሁለት ቀን የማስወረድ ሥነ ሥርዓት ከሆነ፡ የመጀመሪያውን ቀን መጾም የለብዎትም፡ ሁለተኛውን ቀን ግን መጾም  አለብዎ። **እነዚህን የመጾም ሥነ ሥርዓቶች ተከታትለው ካልፈጸሙ ቀጠሮዎ ይሰረዛል።**
- ማስወረዱ የሚደረገው የተወሰነ የሰውነት ክፍልዎን በሚያደነዝዝ እና በመርፌ በሚሰጥ ማደንዘዣ መድኃኒት አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሚያንቀላፉዎት ቢሆንም ሙሉ እንቅልፍ ላይወስድዎ ይችላል፡፡
- የሚሰጡዎ መድኃኒቶች የአዕምሮ ተግባር ውሱንነትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ከማስወረዱ በኋላ ለ24 ሰዓታት መኪና ማሽከርከር እና አጃቢ ሳይኖርዎ በሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ወይም በእግር መጓዝ አይችሉም፡፡
- ወደ ቤትዎ የሚያደርስዎ መኪና መኖሩን ያረጋግጡ፡፡ አጃቢዎ እስከ 4፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ በክሊኒኩ መኖር አለባቸው፡፡
- ወደ ክሊኒኩ አንድ ሰው ይዘው መምጣት ይችላሉ፡፡ ልጆች መምጣት አይፈቀድላቸውም፡፡
- እርግዝናዎ ከ15 ሳምንት በታች ከሆነ በክሊኒኩ የሚኖርዎት ቆይታ ከ2 አስከ 3 ሰዓታት ይሆናል፡፡ እርግዝናዎ 15 ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በክሊኒኩ ከ4-5 ሰዓት ሊቆዩ ወይም በሁለት ቀጠሮዎች መታየት ሊያስፈልግዎና በያንዳንዱ ቀን ለ2 ሰዓት በክሊኒኩ መገኘት ሊኖርብዎ ይችላል፡፡ ወደ ክሊኒኩ ለቀጠሮ ሲደውሉ እንግዳ ተቀባይ በክሊኒክ ስንት ሰዓት መቆየት እንደሚያስፈልግዎ ያውቃሉ።
- ከማስወረዱ በፊት ባለው ሌሊት ወይም ጠዋት ላይ ገላዎን ይታጠቡ ወይም ሻወር ያድርጉ፡፡
- አንዳችም ሽቶ ወይም ኮሎኝ አይቀቡ።
- አጅጌ የሌለውን አንድ ቲ ሸሚዝ አንድ ጥንድ የእግር ሹራቦችን ጨምሮ ሰፋ ያለ ልብስ ይልበሱ።
- በመውሰድ ላይ ያሉትን በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች መውሰድዎን ይቀጥሉ መድሃኒቶችዎንም ይዘው ይምጡ።
- ከቀጠሮዎ በፊት ባሉት 24 ሰዓታት ውስጥ ምንም ዓይነት አስፒሪን (ኤኤስኤ)፣ አልኮል መጠጥ ወይም የተከለከሉ ዕጽዋትን አይውሰዱ፡፡
- ማስወረዱን እስከሚያደርጉበት ቀን ድረስ የደም ምርመራ ውጤትዎን ካላገኘን ቀጠሮዎ ይሰረዛል፡፡
- የጤና መድን ካርድዎንና የመለያ ፎቶዎን ይዘው ይምጡ፡፡ እነዚህን ሳይይዙ ወደ ክሊኒኩ መግባት አይፈቀድልዎትም፡፡
- የጤና መድን ሽፋን ከሌለዎትና ለማስወረዱ ራስዎ የሚከፍሉ ከሆነ ከማስወረዱ ሂደት በፊት ሙሉ ክፍያው መደረግ አለበት፡፡ ክሊኒኩ ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ፣ በዴቢት ካርድ፣ በዋና ክሬዲት ካርዶች፣ በክፍያ ማዘዣዎች ይቀበላል፡፡
- ወደ ማህጸን የሚገቡ የእርግዝና መከላከያዎች፡ ኢቪአርኤ ተለጣፊዎች፡ ኑቫ ቀለበት፡ የድንገተኛ ጊዜ የእርግዝና መከላከያዎችን በክፍያ ይቀርባሉ፡፡

<u>**የማስወረድ ድርጊት አደጋዎች**</u>

1. **በተውሳክ መበከል**
ማህጸን ውስጥ በተውሳክ መበከል (ኤንዶሜትሪቲስ) በመጀመሪያው ሦስት ወር 0.1% ያህል እና በሁለተኛው ሦስት ወር 0.4% ያህል ማስወረዶች ሊያጋጥም ይችላል። በተውሳክ የመበከል ምልክቶች የሚከተሉትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡ የማህጸን መካፈቻ ሕመም፡ ትኩሳት እና መጥፎ ሺታ። ይህ የሚታከመው በአንቲብዮቲክ እና አንዳንዴም ድጋሜ በማስተንፈስ ነው። አአንቲብዮቲክ በደም ሥር መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ሆስፒታል ተኝቶ ምታከም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

2. **ያልተጠናቀቀ ማስወረድ**
ያልተጠናቀቀ ማስወረድ የሚባለው እርግዝናው ሲቋረጥና ነገር ግን ከማሕጸን ውስጥ አንዳች ሥጋ ሳይወጣ ሲቀር ነው። ያልተጠናቀቀ ማስወረድ ምልክቶች ደም መፍሰስን እና የዳጎለ ደም መውጣትን፡ ከባድ ቁርጠትን እና ምናልባትም በተውሳክ መበከልን ይጨምራሉ። ይህ አደገኛ ሁኔታ ካጋጠመ፡ ድጋሜ ማስተንፈስን ያስፈልግ ይሆናል ወይም በክሊኒክ ውስጥ ዲ እና ሲ ወይም ሆስፒታል።

3. **የቀጠለ እርግዝና ወይም ተሞክሮ ያልተሳካ ማስወረድ**
ተሞክሮ ያልተሳካ ማስወረድ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም ነገር አይደለም የሚሆነውም ብዙውን ጊዜ በባዮርኑየት (የተከፋፈለ ወይም የልብ ቅርጽ ያለው) ማሕጸን፡ በጣም ልጅ ሆኖ ማርገዝ፡ ወይም ከማሕጸን ውጭ እርግዝና። አንዳንድ ጊዜ ሐኪሙ እርግዝናውን ለማስወገድ አይችሉም። አሁንም ያረገዘች መሆን ከተሰማት ወይም ማስወረዱ ከተከናወነ በኋላ በ8 ሳምንት ጊዜ ውስጥ የወር አባባዋ ካልመጣ፡ ታካሚዋ ወደ ክሊኒኩ ወይም ሐኪሟ ጋ ተመልሳ መመርመሯ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ ካጋጠመ ሌላ ሙከራ እንዲደረግ ቀጠሮ ሊያዝ ይችላል፡ ወይም ታካሚዋ ወደ ሆስፒታል ልትላክ ትችላለች። አንድ የቱቦ (ከማሕጸን ውጭ) እርግዝና በማስወረድ ካልተቋረጠ በሆድ ላይ ቀድዶ ጥገና ሊወገድ ይችላል።

4. **የማሕጸን መበሳት**
የማሕጸን መበሳት የሚያጋጥመው የማስወረድ ሥነ ሥርዓት በሚከናወንበት ወቅት አንድ መሣሪያ በማሕጸኑ ግድግዳ ውስጥ ሲያልፍ ነው። ይህ ብዙ ጊዜ አያጋጥምም ነገር ግን ካጋጠመ እንደ አንጀት፡ ፊኛ ወይም የደም ሥሮችን የማሳሰሉ የውስጥ አካላትን በመቅደድ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ሕክምናውም አትኩሮ መጠባበቅን፡ ላፓሮስኮፒ ወይም የሆድ ዕቃ ቀዶ ጥገና ማድረግ ሊሆን ይችላል። ባልተለመደ ሁኔታም ሂስቴሬክቶሚ (የማሕጸን ማውጣትን) ሊያስከትል ይችላል።

5. **የማሕጸን መካፈቻ መቀደድ**
የማሕጸን መካፈቻ መቀደድ የሚያጋጥመው ለማስወረድ በሥራ ላይ በሚውል መሣሪያ ነው። መቀደድ በሚቀባ መድሃኒት ሊታከም ይችላል ወይም የማሕጸን መካፈቻን በመስፋት፡ ወይም ሁኒታው ከባድ ከሆነ ለማስተካከል ወደ ሆስፒታል መዘዋወርን ሊያስከትል ይችላል።

6. **የአለርጂ የአለመስማማት ሁኔታዎች**
የአለርጂ የአለመስማማት ሁኔታዎች በውጭ በሚደረግ ማደንዝዣ፡ ማስተኛ፡ ላቴክስ ወይም ከሌሎች ታካሚ ከሚገናኛቸው ሊነሳሱ ይችላሉ። ሊነሳሱ ይችላሉ። አንድ ያለ መስማማት ሁኔታ ከተከሰተ፡ የሕክምና ሠራተኞች መደበኛ የሕክምና ሥር ዓትን በመከተል ታኪሚን ያክማሉ። ከፍተኛ ያለ መስማማት ወደ ሆስፒታል መዘዋወርን ሊያስከትል ይችላል።

7. **የረጋ ደም በማሕጸን ውስጥ መጠራቀም** (ሂማቶሜትራ)
ይህ የሚያጋጥመው ማሕጸን ለማስወጣት ከሚችለው በላይ የደም እርጋታዎች ሲፈጠሩ ሲሆን ይህም ማሕጸን በደም እንዲሞላ ያደርጋል። ይህም ታካሚዋ ሆዷ እንደተነፋ ይሰማታል እንዲሁም ከባድ ቁርጠት ይኖራታል። የዚህ ሕክምናው ደሙን እና የደም እርጋታውን ከማሕጸን ለማስወገድ ድጋሚ ማስተንፈስ ነው።

8. **ከፍተኛ የደም መፍሰስ**
ከፍተኛ የደም መፍሰስ ወይም ከመጠን በላይ መድማት ከማሕጸን መካፈቻ መድማት፡ ከቀረ ሥጋ፡ ዩትሪን አቶይ ወይም መበሳት፡ የደም እለመርጋት እና በሌሎች የማሕጸን ወይም የእትብት ትክክል አለመሆን ሊመጣ ይችላል። ከፍተኛ የደም መፍሰስ በመድሃኒት መታከም፡ በክሊኒክ ውስጥ ድጋሚ ማስተንፈስ ያስፈልግ ይሆናል። ለዲ እና ሲ ወይም ለሌላ ቀድዶ ሕክምና ወደ ሆስፒታል መዘዋወር ደም መሰጠትን ሊያስፈልግ ይችላል።

9. **ሞት**
በተገፊ ማስወረድ ምክንያት ሞት መከተሉ የማይሆን ከቁጥር የማይጋባ ነው። ይህ መወዳደር ያለበት ሙሉውን ጊዜ አርግዛ በመውለድ ወቅት ከሚያጋጥም የሞት አደጋ ጋር ሲሆን ይህ ደግሞ የአጭር ጊዜ እርግዝና ማስወረድ ጊዜ ከሚያጋጥመው አሥራ ሁለት ጊዜ በላይ ነው። ከሁለተኛው የእርግዝና ሲሶ ይልቅ የመጀመሪያው ሲሶ የሚያጋጥም ከማስወረድ ጋእ የተያያዝ ሞት የሚደርስበት ከሁሉም ብላይ የአደጋ ምክንያት የሚሆነው የመርገዣ ዕድሜ ነው። የእነዚህ ሞቶች ምክንያት ከፍተኛ ደም መፍሰስ፡ በተውሳክ መበከል እና ባነስተኛ ሁኔታም ማደንዝዣ ጠቅላላ ማደንዝዣ ደህና እየሆነ ስለመጣና ብዙ በጥቅም ላይ ስለማይውልም ነው።

*መረጃው ከአልታቀደ እና ትክክል ካልሆነ እርግዝና አስተዳደር ̈- ዊሊ ብላክዌል 2009*